# የክራሽን ሞኒተር ሞዴል አጭር ቅኝትና ግምገማ

ሰሎሞን ተሰማ

## 1. መግቢያ

በሁለተኛ ቋንቋ ለመዳ ዙሪያ የሚነሱትን አከራካሪና አወዛጋቢ ጥያቄዎች በሚመለከት የተለያዩ ምሁራን በርካታ ምርምሮችን በማካሄድ የየራሳቸውን መልስ ለመስጠት ሙከራ አድርገዋል፡፡ ከተደረጉት ሙከራዎች መካከል የሁለተኛ ቋንቋ ለመዳን ንድፈ-ሀሳብ በማጠቃለል ሞዴሎችን ለመቅረጽ የተደረጉ ጥረቶች ይገኛሉ፡፡

አንድ የተሟላ ሞዴል ለመቅረጽ ከመሞከሩ በፊት ጥልቅ ጥናትና ምርምር መካሄድ እንዳለበት የታወቀ ነው፡፡ ምርምሩ ደግሞ የተወሰነ መመዘኛን መሠረት ያደርጋል፡፡ ድክመትና ጥንካሬውን የሚነግረንም ይኸው መመዘኛ ይሆናል፡፡

አንድ ሞዴል ሊመዘንና ሊለካ ከሚችልባቸው መመዘኛዎች ጥቂቱ፡-

1. ንድፈ-ሀሳባዊ መሠረቱ÷
2. አጠቃላይነቱና በደንብ መብላላቱ÷
3. የመብራራትና የወደፊቱን ለመጠቆም የመቻል ኃይሉ÷እና
4. ለመረጋገጥ ያለው ብቃት የሚሉት ናቸው (ታደለ 1990÷56)፡፡

ሞዴሎች ምን ያህል እንደተዋጣላቸው የሚረጋገጠውም በመመዘኛዎቹ መሠረት በመገምገምና የተገኘውን ውጤት በመመልከት ይሆናል፡፡

በሁለተኛ ቋንቋ ለመዳ ሂደት ሊነሱ ይችላሉ ብለው የገመቷቸውን ነጥቦች÷ አጠቃላይነት ባለው ሞዴል አማካይነት ለመግለጽና ወጥነት ያለው ንድፈ ሀሳብ ለማቅረብ የሞከሩ ምሁራን በርካታ ናቸው፡፡ የክራሽን 'ሞኒተር ሞዴል'÷ የጋርድነር 'ስትራቴጂ ሞዴል'÷ የኤሊስ 'ቫሪየብል ኮምፒተንስ ሞዴል'÷ የካሮል 'ኮንሸስ ሪኢንፎርስመንት ሞዴል'÷ የላምበርት 'ሶሺአ ሳይኮሎጂካል ሞዴል'÷ የሹመን 'አካልቸሬሽን ሞዴል'÷ የጊልስና ረዳቶቹ 'ኢንተር ግሩፕ (አኮምዴሽን) ሞዴል'÷ የክሊመንት 'ሶሻል ኮንቴክስት ሞዴል' ሁሉ በዚሁ መንገድ የተቀረፁ ሞዴሎች ናቸው፡፡

ታደለ አዳሙ (1990) እንደገለፁት እነዚህ ሞዴሎች ትኩረት እንደ ሚያደርጉበት መሠረታዊ ጉዳይ በሁለት አጠቃላይ ክፍል ሊመደቡ ይችላሉ፡፡ አጠቃላይ ምድቦቹም 1) ማኅበራዊ-ሥነልቦናዊ ሞዴል እና 2) ሥነ-ልቦናዊ ሥነ-ልሳናዊ ሞዴል በመባል ይታወቃሉ፡፡

በዚህ አጠር ያለ ጽሑፍ ለመዳሰስ የተሞከረው ክራሽን 'ሞኒተር ሞዴል' በሚል ስያሜ ያቀረበውን ሞዴል ሲሆን፥ ይህ ሞዴል ሥነ-ልቦናዊ-ሥነ-ልሣናዊ ሞዴል ተብለው ከሚታወቁት ምድብ የሚጠቀስ ነው፡፡

በዚህ ጽሑፍ ሞዴሉ መሠረት የሚያደርጋቸው መላምቶች አጠር አጠር ባለመልክ የተዳሰሱ ሲሆን በመቀጠልም የክርሽንን ሞዴል የሚተቹ ወገኖች ያቀረቧቸውን መከራከሪያዎች በማንሳት ሞዴሉን ለመገምገም ተሞክሯል፡፡ በመጨረሻ ላይም የማጠቃለያ ሀሳብ ተሠንዝሯል፡፡

## 2. የሞኒተር ሞዴል መሠረታዊ መላምቶች

የክራሽን ሞኒተር ሞዴል በ1970ዎቹ መጨረሻ ገደማ በተለያዩ ተከታታይ መጣጥፎች ሲወጣ ከቆየ በኋላ፥ በ1980ዎቹ ውስጥ በተስፋፋ መልኩ በበርካታ መፃህፍት ውስጥ ተብራርቷል፡፡ ይህ ሞዴል ከፍተኛ ታዋቂነት ያገኘና ከወቅቱ ንድፈ-ሀሳቦች ይበልጥ ምሉዕነት ያለው ተደርጎ የሚቆጠር ይሁን እንጂ የዚያኑ ያህል ለከፍተኛ ነቀፋና ሂስ የተጋለጠ ነበር፡፡

የሞኒተር ሞዴል ማዕከላዊ ጭብጥ የሆኑት አምስቱ መላምቶች፡-

2.1 ቋንቋ መልመድ-መማር መላምት፥
2.2 ተፈጥሮአዊ ቅደም ተከተል መላምት፥
2.3 ሞኒተር መላምት፥
2.4 ግብዓት መላምት፥
2.5 ተጽዕኖ ማሳደር-ማጣራት መላምት ናቸው፡፡

### 2.1 ቋንቋ መልመድ - መማር መላምት

ክራሽን በዚህ መላምቱ በመልመድና በመማር መካከል ልዩነት መኖሩን አሳይቷል፡፡ በርሱ ግምት ዐዋቂዎች የሁለተኛ ቋንቋ ችሎታቸውን የሚያዳብሩባቸው ሁለት የተለያዩና ራሳቸውን የቻሉ መንገዶች አሉ፡፡ እነዚህም በማስተዋልና በግንዛቤ ላይ ያልተመሰረተ (subconscious) የቋንቋ

ለመዳና በማስተዋልና በግንዛቤ ላይ የተመሠረተ (conscious) የቋንቋ ትምህርት ናቸው (ክራሽን፥ 1982፡10)።

### 2.1.1 ቋንቋ መልመድ

በመላምቱ መሠረት መልመድ ማለት ተፈጥሮአዊ በሆነ የመግባባት ሂደት ለማጁ የቋንቋ ችሎታውን የሚያሳድግበት ሂደት ማለት ነው።

ይህ የቋንቋ ለመዳ ሂደት ሙሉ በሙሉ አንድ ባይሆንም ሕፃናት የአፍ መፍቻ ቋንቋቸውን ከሚለምዱበት ሂደት ጋር ተመሣሣይ ነው። እንደክራሽን አመለካከት፥ ቋንቋ ለመዳ በግንዛቤ ላይ የተመሠረተ ሂደት አይደለም። የቋንቋ ተማሪውም በዚህ ሂደት የሚያልፍ እስከሆነ ድረስ ስለቋንቋው ልዩ ልዩ ባህርያት ጠንቅቆ ማወቅ አይጠበቅበትም። ነገር ግን እነዚህን ባህርያት ባይለይም፥ በቋንቋው መግባባት መቻሉን ይገነዘባል፤ በስሜት (feeling) ብቻም ሰዋስዋዊ አገባቦች ልክ መሆን አለመሆናቸውን ሊለይ ይችላል። የመልመድ ሂደት ተፈጥሮአዊ በሆነ የመግባባት ሂደት ውስጥ በመስተጋብር የሚላበሱት እንደመሆኑ መጠን ተጠቃሚዎች ለመልዕክታቸው ፍቺ (meaning) እንጂ ለቅርጽ (form) ትኩረት አይሰጡም። ስሕተትንም ሆን ብሎ በዝርዝር ለመከታተልና ለማረም የሚደረግ ጥረት አይኖርም። ስሕተትን ማረም ራሱ በመልመድ ሂደት ላይ ምንም ዓይነት ተጽዕኖ አይኖረውም።

### 2.1.2 ቋንቋ መማር

በመላምቱ መሠረት መማር፥ ሆን ብሎና አቅዶ የቋንቋ ሕግጋትን ዝርዝር በማጥናትና ስሕተትንም በማረም ቋንቋን የራስ ለማድረግ መቻሉን ይገልፃል።

በክራሽን አመለካከት ቋንቋን መማር ማለት ሕግጋትን ማወቅ፥ ስለ ሰዋስው በግንዛቤና በማስተዋል ላይ የተመሠረተ ዕውቀት ማግኘት ማለት ነው። በመማር ሂደት ስሕተትን ማደንና ማረም ማዕከላዊ ጉዳይ ነው። ለዚህም ዓይነተኛ ምሳሌ የሚሆነው የክፍል ውስጥ መደበኛ የቋንቋ ሕግጋት ዝርዝር ጥናት ነው (ማክላውሊን፥ 1991፡20)። በክራሽን ግምት መልመድና መማርን የሚለየው የቋንቋ ለመዳው የሚካሄድበት ቦታ ሳይሆን በግንዛቤ ላይ የተመሠረተና ያልተመሠረተ የመሆኑ ትኩረት ነው።

ክራሽን መማር ወደ መልመድ አይሸጋገርም (Learning does not turn into acquisition) ባይ ነው። ሕግጋትን በማቅረብና ሰዋስውን በማብራራት በግንዛቤና በማስተዋል ላይ የተመሠረተ ትምህርት (conscious rule learning)

ለቋንቋ መልመድ መሠረት ሊሆን አይችልም ክራሽን፥ (ገጽ 85-86)። ለዚህ አስተያየቱ መሠረት የሚያደርገው የሚከተሉትን ሦስት ዋና ዋና ጉዳዮች ነው።

1) አንዳንድ ጊዜ ቋንቋን ሳይማሩት መልመድ ይቻላል። ለዚህም ማስረጃው፥ ሰዎች የታላሚውን ቋንቋ ሕግጋት በአግባቡ ሳይለዩ ነገር ግን በቋንቋው ለመጠቀም በቂ ችሎታ ሲኖራቸው ማየት መቻሉ ነው፤

2) ሌሎች ደግሞ የቋንቋውን ሕግጋት በሚገባ ተምረውም እያሉ ግልጽና ቀላል የሆኑ ስሕተቶችን ይሰራሉ። ይህም መማራቸው ስሕተት ላለመስራት ምክንያት ሊሆናቸው አለመቻሉን ያሳያል፤

3) ማንም ሰው የአንድን ቋንቋ ሕግጋት በሙሉ ሊያውቅ አይችልም። ይህም መልመድ ከመማር በኋላ የሚገኝ ነው በሚለው አተያይ ላይ ጥርጣሬ ያስከትላል።

አንዳንድ ወገኖች ሕፃናት ቋንቋን ይለምዳሉ፤ ዐዋቂዎች ደግሞ ይማራሉ የሚል ግንዛቤ አላቸው። በክራሽን መላምት መሠረት ግን ዐዋቂዎችም ቋንቋን ይለምዳሉ ማለት ይቻላል። ቋንቋን መልመድ ዕድሜ እየገፋ ቢሄድም እንኳን የሚቋረጥ ሂደት አይደለም።

## 2.2 ተፈጥሮአዊ ቅደም ተከተል መላምት

በሁለተኛ ቋንቋ ለመዳ ምርምር ውስጥ አስደናቂ ግኝት ተደርጎ የሚወሰደው፥ በለመዳ ሂደት ይታያሉ ተብለው የሚገመቱ ቅደም ተከተሎች መኖር ነው።

ክራሽን የሁለተኛ ቋንቋ ለማጆች የአንድን ቋንቋ ሰዋስዋዊ ባህርያት በሚለምዱበት ወቅት የሚከተሉት ተፈጥሮአዊ የሆነ ቅደም ተከተል አለ ይላል። የሁለተኛ ቋንቋ ለማጆችን የአለማመድ ሁኔታ ሲከታተልም የተወሰነ መመሳሰል እንዳጋጠመውና የተወሰኑ አገባቦች ከሌሎች ቀድመው እንደሚለመዱ ይገልፃል።

በመላምቱ መሠረት፥ ቋንቋን የምንለምደው በተወሰነ ቅደም ተከተል መሠረት ነው። አንዳንድ ሕግጋት ቀደም ብለው፤ ሌሎች ደግሞ ዘግየት ብለው ይዋሃዱናል። በክፍል ውስጥ የቋንቋ ትምህርት የተከታተሉም ሆኑ ከክፍል ውጪ ቋንቋን የለመዱ፥ ይህንኑ ቅደም ተከተል እንደሚከተሉም

ተረጋግጧል። ይህ የአለማመድ ሂደት መቶ በመቶ በሁሉም ግለሰብ ዘንድ ተመሣሣይ ባይሆንም መሠረታዊ የሆነ መመሣሠል ግን ይታያል። በዚህ መላምት ረገድ ጠለቅ ያለ ጥናት የተደረገበት ቋንቋ እንግሊዝኛ ሲሆን ከርሱም ይበልጥ የተጠናው የምዕላድ ክፍል ነው (ክራሽን 12)።

ማክላውሊን (ገጽ 31) እንደጠቀሰው፥ ዱሌይና በርት በ1974 ባደረጉት አንድ ጥናት፥ የእንግሊዝኛ ቋንቋ ምዕላዶችን በመማር ሂደት የተወሰነ ቅደም ተከተል እንዳለ ለማየት ሞክረዋል። ክራሽንም ቢሆን ከምዕላድ ባሻገር የተወሰነ የአለማመድ ቅደም ተከተል እንዳለ ለማስረዳት ይሞክራል።

ሊትልውድ (1984፥ 9-10) ብራውንን (1973) ጠቅሶ እንዳመለከተው፥ በ3 ሕፃናት የምዕላድ አለማመድ ሂደት ላይ በተካሄደ ጥናት መሠረት የሚከተሉት 14 የእንግሊዝኛ ምዕላዶች በቀረቡበት ቅደም ተከተል መሠረት እንደሚለመዱ አሳይቷል።


1. present progressive *-ing* (as in she is running)
2. preposition *-on*
3. preposition- *in*
4. plural *-s* (as in two books)
5. irregular past form (as in she went)
6. possessive '*s* (as in daddy's hat)
7. uncontractible copula (eg. *'is'* in yes, she is)
8. articles 'the' and '*a*' (which were classified together)
9. regular past - *ed* (as in she walked)
10. regular third-person-singular *-s* (as in she runs)
11. irregular third-person-singular forms (eg. she has)
12. uncontractible auxiliary '*be*' (as in she was coming)
13. contractible copula (as in she's tired)
14. contractible auxiliary '*be*' (as in he's coming)

በዚሁ መሠረት በክራሽን አባባል የሰው ልጅ ቋንቋን በሚለምድበት ወቅት ተፈጥሯዊ የሆነ የአለማመድ ቅደም ተከተል አለ ማለት ነው።

## 2.3 ሞኒተር መላምት

ሞኒተር፥ የቋንቋ ለማጁ ውስጣዊ ሥርዓት ሲሆን ይህም ወደ ቋንቋ ለማጁ የሚደርሰውን መልዕክት የሚቆጣጠር ነው።

የሞኒተርን ሥርዓት ከሚከተለው መግለጫ መገንዘብ ይቻላል።




<u>ምንጭ</u>:- (ዱላይና ሌሎች፥1982:46)

የሞኒተር መላምት እንደሚያስገነዝበው አንድ ተናጋሪ ሀሳቡን ከማፍለቁ በፊት አርትኦት ('edition') ያካሂዳል። ለአርትኦቱም የሚጠቀመው በማስተዋልና በግንዛቤ ላይ የተመሠረተውንና የተማረውን ዕውቀት ነው።

ሞኒተር ከቋንቋ መልዕክት ይልቅ በአገባብና በቅርጽ ላይ ቁጥጥር የሚያደርግ ሲሆን የዚህ መላምት መሠረተ-ሀሳብ መልመድና መማር የሚያገለግሉት በተለያየ መንገድ መሆኑን ያረጋገጠ ነው (ክራሽን 15)። መልመድ በቋንቋው መነጋገርን የሚያነሳሳና ለርቱዕነት ወሳኝ ሲሆን፤ መማር ግን ያለው ተግባር ራስን ማረም ወይም መቆጣጠር ይሆናል። ይህም ማለት የተማርነው ሁሉ ሥራ ላይ የሚውለው፥ በመልመድ ሥርዓት ያወቅነውን ማፍለቅ ስንጀምር፤ የዚያን ንግግር ቅርጽ ለመቀየርና ለመለወጥ ይሆናል ማለት ነው። አንድ ተማሪ ቋንቋውን ሲጠቀም ስሕተት ላለመስራት ራሱን መቆጣጠር ሲጀምርና አጠቃቀሙን ሁሉ ሆን ብሎና አውቆ ሲከታተል የሞኒተር ሥርዓቱን እየተጠቀመበት ነው ማለት ይቻላል። በዚህ ወቅት የተስተካከሉ ዐረፍተ ነገሮችን በጥንቃቄ ያፈልቃል፤ ንግግሩንና ጽሑፉን ያርማል።

ሞኒተርን የመጠቀም ደረጃ (ዱላይና ሌሎች 59)፡-

1) በተማሪው ዕድሜ፥
2) በተማሪው መደበኛ ትምህርት ደረጃ፥
3) ንግግሩ/ጽሑፉ በሚቀርብበት ሁኔታ፥
4) በቋንቋው ተጠቃሚ ግለ-ሰብዕና ላይ ሊመሠረት ይችላል፡፡

አንድ ሰው የሞኒተር ችሎታውን በአጥጋቢ ሁኔታ ለመጠቀም ሦስት ሁኔታዎች ያስፈልጉታል፡፡ እነዚህም ሁኔታዎች፡-

1) ጊዜ (time)፡- የቋንቋውን ሕግጋት በደንብ አስቦ በአግባቡ ለመጠቀም የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪው በቂ ጊዜ ሊያገኝ ይገባል፡፡ ይሁንና፥ በዕለት ተዕለት የንግግር ሂደት ወቅት ብዙ ሰዎች ስለሚጠቀሙበት ቋንቋ የሚያስቡበት በቂ ጊዜ የላቸውም፡፡ ይህም ሆኖ ግን በዚያው ቅጽበት ሕግጋቱን በግንዛቤ ለመጠቀም ከሚያደርጉት ጥረት የተነሳ በንግግር ሰዓት መወላወል፥ እ...እ...ማለት፥ የሌላውን ወገን ንግግር አለማዳመጥ ሁሉ ይታይባቸዋል፡፡

2) በቅርጽ ላይ ማተኮር (focus on form)፡- አንድ የሁለተኛ ቋንቋ ተጠቃሚ የሞኒተር ሥርዓቱን በአግባቡ ለመጠቀም እንዲችል ከተፈለገ፥ "ጊዜ" ብቻውን በቂ አይደለም፡፡ የቋንቋው ተጠቃሚ በቅርጽ ላይ ሊያተኩር፥ ስለሚያፈልቀው ቋንቋ ትክክለኛነት በአግባቡ ሊያስብ ይገባዋል፡፡

3) ሕግጋትን ማወቅ (know the rules)፡- አንድ የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪ ሞኒተርን ለመጠቀም በጊዜና በቅርጽ ላይ ከማተኮር ባሻገር የቋንቋውን ሕግጋት ማወቅ ይኖርበታል፡፡ ይሁን እንጂ ማንም ቢሆን የአንድን ቋንቋ ሕግጋት ሙሉ በሙሉ ለማወቅ የሚቻለው አይሆንም፡፡ ተማሪዎችም ሊማሩ የሚችሉት ከአንድ ቋንቋ አጠቃላይ የሰዋስው ህጎች መካከል ጥቂቱን ነው፡፡

ክራሽን (ገጽ 19) ሞኒተርን በመጠቀም ረገድ ግለሰቦችን በሦስት ከፍሎ ለማየት ሞክሯል፡፡

1) ሞኒተርን ከሚገባው በላይ የሚጠቀሙ፡- አንዳንድ ሰዎች ሞኒተርን ከሚገባው በላይ አዘውትረው ለመጠቀም ሲሞክሩ ይታያል፡፡ እንዲህ ዓይነቶቹ፥ ባላቸው የሁለተኛ ቋንቋ ዕውቀት መሠረት ሀሳባቸውን በተደጋጋሚ የሚፈትሹ ናቸው፡፡ እንዲህም በማድረግ ንግግራቸውን ለማረቅና ራሳቸውን ለማረም ስለሚሞክሩ እንደበተ-ርቱዕ ሆነው ለመናገር ይቸገራሉ፡፡

ራሳቸውን በራሳቸው ከሚገባው በላይ ስለሚቆጣጠሩም ብዙውን ጊዜ ወደኋላ ይቀራሉ::

ሞኒተርን ከሚገባው በላይ ለመጠቀም ምክንያቱ ብዙ ሊሆን ይችላል:: ለምሳሌ፥ የማስተማር ስልት አንዱ ሆኖ ሊጠቀስ ይችላል:: በሰዋስው ዝርዝር ጥናት ላይ በተመሠረተ የቋንቋ ትምህርት ሥር ያለፉ ተማሪዎች ለእንደዚህ ዓይነቱ ሁኔታ የተጋለጡ ናቸው:: የግለሰቦች ማንነትም (personality type) ራሱ ለእንዲህ ዓይነቱ ሁኔታ ሊያጋልጥ ይችላል:: አንዳንድ ግለሰቦች ቋንቋውን ለመልመድ ዕድሉ እያላቸውም እንኳ ሀሳባቸውን ለመግለጽ እርግጠኛ የሚሆኑት በሚያውቁት ሕግ መሠረት ሲያርቁና ሲያስተካክሉ ብቻ ስለሚመስላቸው፥ አዘውትረው ሞኒተርን ሲጠቀሙ ይታያሉ:: እንዲህ ዓይነቶቹ፥ ሞኒተርን ከሚገባው በላይ ለመጠቀም የሚሞክሩ ሰዎች ብዙውን ጊዜ የሚያልፉት በመማር ሂደት ውስጥ ነው::

2) <u>ሞኒተርን ከሚገባው በታች የሚጠቀሙ</u>:- እንዲህ ያሉት ሰዎች በአብዛኛው ያልተማሩ፥ ወይም ቢማሩም፥ ሁኔታው ፈቅዶላቸው እንኳን በግንዛቤ ላይ የተመሠረተ ዕውቀት ለመጠቀም የማይመርጡ ናቸው:: በዚህ ምድብ የሚካተቱት በአመዛኙ ስሕተትን ለማረም የማይጨነቁና ለስህተትም ያልተጋለጡ ናቸው:: ስሕተታቸውን የሚያርሙት ማረም የሚያስፈልግ መስሎ ሲታያቸው ብቻ ሲሆን፥ ይበልጥ የሚያዘነብሉትም በመልመድ ሂደት ላይ ነው::

3) <u>ሞኒተርን በተፈላጊው ደረጃ የሚጠቀሙ</u>:- እንደዚህ ያሉት ደግሞ ግንኙነትን በማይነካ መልኩ ሲያስፈልጋቸው ብቻ ሞኒተርን የሚጠቀሙ ናቸው:: አጠቃቀማቸውም ቢሆን መግባባትን የሚያደናቅፍ አይደለም:: በዚህ ደረጃ ሞኒተርን የሚጠቀሙ ሰዎች ጊዜ ሲኖራቸው በጽሕፈትና በንግግር ወቅት የቋንቋ አጠቃቀም ትክክለኛነት ደረጃቸውን ከፍ ለማድረግ አስፈላጊውን እርማት ሲያካሂዱ ይታያሉ:: በትምህርት ፕሮግራም ውስጥም ዋነኛ ግቡ ሞኒተርን በዚህ ደረጃ የሚጠቀሙ ግለሰቦችን ማፍራት ይሆናል:: በክራሽን አመለካከት (ማክላውሊን፥ 27) ሞኒተርን ከተገቢው በላይ የሚጠቀሙ ሰዎች ለሰዋስው ትምህርት የተጋለጡ ወይም ቋንቋን በሕግጋት ጥናት መሠረት ለመማር ፍላጎት ያላቸው ሲሆኑ፥ በተቃራኒው ከተገቢው በታች የሚጠቀሙት ደግሞ በግንዛቤና በማስተዋል ላይ የተመሠረተ የቋንቋ ሕግን ፈጽሞ የማይጠቀሙ ወይም በጣም በጥቂቱ የሚጠቀሙ ናቸው::

## 2.4 የግብዓት መላምት

በክራሽን የግብዓት (input) መላምት አመለካከት፥ አንድ የቋንቋ ተማሪ (ለማጅ) ቋንቋን የሚለምደው ባለው የቋንቋ ችሎታ ላይ አዲስ የሆነ የተወሰነ ግብዓት ሲጨምር ነው:: ይህን አስተያየት ክራሽን (ገጽ 20)i ⟶ i+1 በሚል ቀመር ይገልፀዋል:: እንደክራሽን ገለፃ የቋንቋው ለማጅ በታላሚው ቋንቋ ለመዳ ሂደት ወደሚቀጥለው ደረጃ ለመሸጋገር በሚለመደው የቋንቋ ክፍል ውስጥ ሊኖር የሚችለውን አገባብ ያካተተ የቋንቋ ግብዓት መረዳት ይኖርበታል::

የሰው ልጅ ቋንቋን የሚለምደው በአንድ መንገድ ነው:: ይኸውም የተሟላ ግብዓት (comprehensible input) ሲቀርብለትና፣ የሚተላለፈውን መልዕክት ሲረዳ ነው:: በአንድ ወቅት ካለበት የቋንቋ ዕውቀት ደረጃ (i) ወደሚቀጥለው ደረጃ (i+1) የሚሸጋገረው ተፈጥሮአዊ በሆነ ቅደም ተከተል መሠረት ነው:: በሌላ አባባል ክራሽን እንደሚገልፀው፥ ቋንቋን የሚለምደው አሁን ካለበት ደረጃ ትንሽ ለጠቅ ያለ አገባብ ያዘለ ቋንቋ መረዳት ሲጀምር ነው::

ክራሽን የግብዓት መላምትን አስመልክቶ፥ አንደኛ፥ የግብዓት መላምት ከቋንቋ መማር ጋር ሳይሆን ከቋንቋ ለመዳ ጋር የተያያዘ ነው፤ ሁለተኛ፥ ቋንቋን በመረዳት ልንለምደው የምንችለው በተወሰነ ደረጃ ላይ ከምናውቀው በተጨማሪ አዲስ ነገር ሲኖረው ነው፤ ሦስተኛ፥ ቋንቋን ማፍለቅ ያሚከሰት እንጂ በቀጥታ የሚማሩት አይደለም በማለት አመለካከቱን አጠቃሏል:: ለክራሽን (ማክላውሊን፥36) የተሟላ ግብዓት ወደመልመድ የሚያደርስ መንገድ ሲሆን፥ ግብዓቱ የሚረዱት እስከሆነ ድረስ የታላሚው ቋንቋ ሰዋስው ወዲያውኑ የሚታወቅ ይሆናል::

ክራሽን የግብዓት መላምቱን የመሠረተባቸው ማስረጃዎች የሚከተሉት ናቸው::

1) <u>የዝምታ ወቅት (silent period)</u>:- ሕፃናት አንድን ቋንቋ ለምደው መጠቀም (መናገር) ከመጀመራቸው በፊት የተወሰነ ጊዜ በዝምታ ያሳልፋሉ:: ይህ ወቅት የተሟላ ግብዓት የሚያዳብሩበት ወቅት ሲሆን፥ ይህ ችሎታ አንዴ ከተመሠረተ ንግግሩን በቀላሉና ወዲያውኑ ማፍለቅ ይጀምራሉ::

2) <u>የዕድሜ ልዩነት (age difference)</u>:- ዐዋቂዎች ከሕፃናት ይልቅ የተሟላ ግብዓት መቀበል ስለሚችሉ በመጀመሪያዎቹ ደረጃዎች ለመልመድ ፈጣን ናቸው:: ግብዓቱ ለዐዋቂዎች የተሟላ የሚሆንበት ምክንያትም፥

ከሕፃናት ይልቅ ስለአካባቢያቸው ያላቸው ዕውቀት ግብዓቱን ትርጉም አዘል ስለሚያደርግላቸው ነው።

3) ለሁኔታዎች የመጋለጥ ሁኔታ (the effect of exposure) - ሰዎች ቋንቋ በሚነገርበት አካባቢ ብዙ በቆዩ ቁጥር ቋንቋውን በደንብ እየለመዱት ይመጣሉ። ለክራሽን፥ ይህ ማለት፥ ለቋንቋው መጋለጥ ብቻ ሳይሆን፥ ለተሟላ ግብዓት መጋለጥንም ይጨምራል።

4) የተሟላ ግብዓት አለማግኘት (lack of access to comprehensible input):- የተሟላ ግብዓት በሌለበት ቦታ የሕፃናት ቋንቋ ለመዳ የዘገየ ይሆናል። ክራሽን ይህን ሁኔታ እንደተመለከተው፥ መናገርና ማዳመጥ የማይችሉ ወላጆች ያሏቸው ሕፃናት አዝጋሚ የቋንቋ ዕድገት ሲያሳዩ፥ ወላጆቻቸው እንዲህ ቢሆኑም እንኳን፥ ከሌሎች ሕፃናትና ሰዎች ጋር ለመቀራረብ ዕድል ያላቸው ሕፃናት ደግሞ የቋንቋ ለመዳ ፍጥነታቸው ይጨምራል።

5) ቋንቋን ሙሉ በሙሉ ተዋህዶ መማር (immersion and sheltered language teaching):- ተማሪዎች ሙሉ በሙሉ ተዋህዶ በመማር ዘዴ የሚጠቀሙ ከሆነ፥ ለተሟላ ግብዓት የተጋለጡ ስለሚሆኑ፥ የተሻለ የቋንቋ ችሎታ ይኖራቸዋል። የዚህ ዓይነቱ የትምህት ፕሮግራም የተሳካ መሆን ለተሟላ ግብዓት አስፈላጊነትና ምንነት እንደማስረጃ ሊጠቀስ ይችላል።

6) የልሣነ-ክልዔ መርሀ-ግብር መሳካት (the success of bilingual programmes):- ክራሽን እንደሚለው፥ ልሣነ-ክልዔ የሆኑ መርሀ-ግብሮች የተሳኩ የሆኑ እንደሆን ለተማሪዎች የተሟላ ግብዓት ስለሚሰጧቸው ሁለተኛ ቋንቋን የመማር ችሎታቸው ውጤታማ ይሆናል።

7) የማንበብ መላምት (The reading hypothesis):- የጥሩ ጽሕፈት ችሎታ መሠረቱ፥ ለመዝናናትም ሆነ ለግል ፍላጎት በራስ አነሳሽነት የሚደረግ መጠነ-ሠፊ ንባብ ነው ተብሎ ይገመታል። እንዲህ ዓይነቱ ንባብ ለግለሰቡ የተሟላ ግብዓት ስለሚፈጥርለት የመፃፍ ስሜቱ ሊነሳሳ ይችላል (ማክላውሊን 37-43)።


## 2.5. ተጽዕኖ ማሳደርና ማጣራት መላምት

ክራሽን በዚህ መላምቱ፥ በቋንቋ መማር ሳይሆን በቋንቋ መልመድ ሂደት ተጽዕኖ ሊያሳድሩ ይችላሉ ያላቸውን ማኅበራዊና ሥነ-ልቦናዊ ሁኔታዎች አመልክቷል፡፡ ከሥነልቦናዊ ገፅታ አንፃር፥ በእርሱ አስተያየት፥ አመለካከት (attitude)፥ ማነሳሻ (motivation)፥ በራስ መተማመን (self confidence)፥ ጭንቀት (anxiety)፥ እና የመሳሰሉት፥ ተጽዕኖ የሚያሳድሩትን ሁኔታዎች ይመሠርታሉ፡፡ እነዚህ ሁኔታዎች ወደቋንቋ ለማጁ ሊደርስ የሚችለውን ግብዓትና፥ ደርሶትም በራሱ የቋንቋ ሥርዓት ውስጥ ሊያካትተው የሚችለውን መጠን ይወስናሉ (ክራሽን 31)፡፡

እንደመላምቱ አቀራረብ፥ የቋንቋ ለመዳውን ሂደት የሚያግዱና ተጽዕኖ የሚያሳርፉ ሁኔታዎች እስካሉ ድረስ የተሟላ ግብዓት ብቻውን ለሁለተኛ ቋንቋ ተማሪው የቋንቋ ለመዳ የሚረዳው አይሆንም፡፡ ክራሽን ራሱ እንደሚገልፀው፥

> ግብዓት ለሁለተኛ ቋንቋ ለመዳ የመጀመሪያው ወሳኝ ሁኔታ ነው፡፡ ተጽዕኖ የሚያሳድሩ ሁኔታዎች ደግሞ ግብዓት ቋንቋ መልመጃ ወደሆነው አእምሮአዊ ክፍል (LAD) እንዳይደርስ ሊያግዱ ወይም በፍጥነት እንዲደርስ ሊያቀላጥፉ ይችላሉ (ክራሽን፡32)፡፡

ክራሽን ይህን አመለካከት በሚከተለው መልክ ይገልፀዋል፤



የተጽዕኖ ማሳደርና ማጣራት መላምት መሠረተ-ሀሳብ ለመጀመሪያ ጊዜ የቀረበውና የሁለተኛ ቋንቋ ለመዳን የሚነኩ ተውላጦች (variables) ምን እንደሆኑ ለማየት የተሞከረው በዱላይ እና በርት ነው (ማክላውሊን 53)። ጽንሠ-ሀሳቡ ይበልጥ የተመረመረው ደግሞ በዱላይ፥ በርትና ክራሽን ነው።

በሌላም በኩል ማጣራት (filter) አራት ተግባራት ያሉት ሲሆን ተግባራቱም የሚከተሉት ናቸው።

1) ተማሪው የትኛውን የቋንቋ ሞዴል መምረጥ እንዳለበት ይወስናል።
2) ከቋንቋው ክፍሎች መካከል የትኛው ቀድሞ መለመድ እንዳለበት ይወስናል።
3) የቋንቋ ለመዳ ጥረቱ መቼ እንደሚቋረጥ ይወስናል።
4) ተማሪው አንድን ቋንቋ በምን ያህል ፍጥነት ሊማረው እንደሚገባ ይወስናል።

በክራሽን ትንታኔ መሠረት የማጣራቱ ደረጃ ዝቅተኛ ሲሆን የቋንቋው ግብዓት ወደለማጁ የቋንቋ መልመጃ አእምሮአዊ ክፍል (LAD) ደርሶ የቋንቋ ዕውቀቱ አካል ይሆናል። ማጣራቱ ከፍተኛ ሲሆን ግን፥ ግብዓቱ ስለሚታገድ የቋንቋ መልመጃው አእምሮአዊ ክፍል ዘንድ የመድረስ አቅሙ ይቀንሳል። በሌላ አባባል መሠናክሉቹ አነስተኛ የሆኑለት ተማሪ ብዙ መልመድ ሲችል ከፍተኛ የሆኑበት ደግሞ የሚለምደው አነስተኛ ይሆናል።

በርሱ አመለካከት በሁለተኛ ቋንቋ ለመዳ ረገድ የሚታየው የግለሰቦች ልዩነት መሠረቱ እነዚሁ በለመዳው ላይ ተጽዕኖ የሚያሳርፉ ሁኔታዎች ናቸው። ቀደም ሲል እንደተጠቆመው በሁለተኛ ቋንቋ ለመዳ ወቅት ተጽዕኖ ሊያሳርፉ ይችላሉ ተብለው ከሚቆጠሩት መካከል አንዱ ማነሳሻ (motivation) ነው። ማነሳሻ በዋናነት በሁለት ተከፍሎ ሊታይ ይችላል። አንደኛው የማነሳሻ ዓይነት የትስስር ማነሳሻ (Integrative motivation) ሲሆን ሁለተኛው ዓይነት ደግሞ የተጠቃሚነት ማነሳሻ (Instrumental motivation) ነው።

<u>የትስስር ማነሳሻ</u>፡- ይህ ማነሳሻ የሚገልፀው፥ አንድ ሰው በሁለተኛው ቋንቋ ጥሩ ችሎታ እንዲኖረው የሚፈልገው ከቋንቋው ተናጋሪዎች ጋር ለመቀራረብና በእነርሱ ሕይወት ውስጥ ተሣታፊ ለመሆን መሆኑን ነው። ይህም በሌሎች ሕዝቦች ባህልና ቋንቋ ላይ ከልብ የመነጨ ግለሰባዊ ፍላጎት ማሳደርን ይመለከታል።

በሦስተኛ የማነሳሻ ዓይነትነት የሚጠቀሰው የአንድ ማኅበራዊ ቡድን አባልነትም (social group identification) እንደ ትስስር ማነሳሻ ሁሉ የቋንቋ ለማጁን ፍላጎት ሊወስን ይችላል:: የሁለተኛ ቋንቋ ለማጁ በሚለምደው ቋንቋ ተናጋሪዎች ማኅበራዊ ቡድን ውስጥ አባል ከሆነ ቋንቋውን ለመልመድ ይገፋፋል:: ይህ ካልሆነ ደግሞ አይገፋፋም ተብሎ ይገመታል::

<u>የተጠቃሚነት ማነሳሻ</u>:- ይህ ማነሳሻ የሚገልፀው ደግሞ አንድ ሰው በሁለተኛው ቋንቋ ጥሩ ችሎታ እንዲኖረው የሚፈልገው የተወሰነ ሥራ ለመሥራትና የተወሰነ ጥቅም ለማግኘት ሲል መሆኑን ነው:: ይህም የሚሆነው ከራስ በመነጨ ውስጣዊ ፍላጎት ሳይሆን ከጥቅም በመነጨ ሁኔታ መሆኑን ያመለክታል (ዱላይና ሌሎች 47-51)::

ሁሉም ዓይነት ማነሳሻዎች በሁለተኛ ቋንቋ ለመዳ ፍጥነት ላይ የየራሳቸው ተጽዕኖ ሲኖራቸው፥ ከመካከላቸው አንዱ ደግሞ በተወሰነ ሁኔታ ውስጥ የጎላ ተጽዕኖ ሊያሳድር የሚችል ይሆናል:: ስሜታዊ ሁኔታዎችም በተመሳሳይ ሁኔታ በቋንቋ ለመዳው ላይ የጎላ ተጽዕኖ ያላቸው ናቸው:: የተዝናና ስሜት ያላቸውና በራሳቸው የሚተማመኑ ሰዎች ቋንቋን በቀላሉ ለመልምድ የተመቻቸ ዕድል ሲኖራቸው ጭንቀት የሚያበዙና በራሳቸው የማይተማመኑ ደግሞ የሞኒተር ሥርዓታቸው ከፍተኛ ስለሚሆን ለቋንቋ ለመዳ የተመቻቸ ሁኔታ የላቸውምና የለመዳው ሂደት የተደናቀፈ ይሆንባቸዋል:: በአጠቃላይ ሰዎች የሚሰሙትን ሁሌ የሚቀበሉ አይደሉም:: ፍላጎታቸው፥ አመለካከታቸውና ስሜታቸው የማጣራትና የማገድ ተግባር ስለሚፈጽም የሚማሩትን ቋንቋ የማወቅን ፍጥነትና ጥራት በቀጥታ ይነካዋል::

ክራሽን፥ ከዚህ በላይ ባየናቸው መላምቶቹ የሠነዘራቸው አስተያየቶች አነሳስተዋቸው የምርምር ሥራ በማካሄድ የርሱን አስተያየት ያጠናከሩ ምሁራን ሲኖሩ፥ የዚያኑ ያህል በመላምቶቹ ላይ ጥያቄ በማንሳት ጠንካራ ሂስ የሰነዘሩበት አጥኚዎች ይገኛሉ:: ከዚህ በመቀጠልም በመላምቶቹ ላይ የሚሰነዘሩትን ትችቶች በአጭር በአጭሩ ለማየት እንሞክራለን::

## 3. የግምገማ አስተያየት

ማክላውሊን (ገጽ 21) እንደገመገመው፥ ክራሽን በግንዛቤ ላይ የተመሠረተ (conscious) እና በግንዛቤ ላይ ያልተመሠረተ (subconscious) የሚሉትን ቃላት ለመማርና መልመድ መግለጫነት ይጠቀምባቸው እንጂ ብያኔውን በግልጽ አላሳየም:: በመማርና በመልመድ መካከልም በሙከራ ሊረጋገጥና ሊፈተን የሚችል ልዩነት አላመለከተም::

ክራሽን መልመድና መማርን ባብራራበት መልኩ ሙሉ በሙሉ ለይቶ ማቅረቡ ራሱ ተገቢ አይደለም (ኤሊስ፥ 1985፡ 264-65)። መማርም ቢሆን ወደ መልመድ ሊሽጋገር አይችልም ይበል እንጂ፥ በተግባር እንደሚታየው በመማር የተቀሰመ ዕውቀት በልምምድ ወደመልመድ እንደሚሽጋገር ማረጋገጥ ይቻላል። ኤሊስ፥ ላርሰን ፍሪማንን በመጥቀስ እንደገለፀው፥ በክራሽን አመለካከት እንስማማ ብንል እንኳን የመልመድና የመማር ልዩነት ዓይነተኛ ከሆነ፥ አንዱ ከአንዱ እንዴት እንደሚለይና ለእያንዳንዱ ተጠያቂነት ያለው ዕውቀት የቱ እንደሆነ ማመልከት የግድ ይሆናል። ይሁንና ክራሽን ይህን ማድረግ አልተቻለውም።

የክራሽን ተፈጥሮአዊ ቅደም ተከተል መላምት ለግለሰቦች የቋንቋ አለማመድ ልዩነት ብዙም ግምት የሚሰጥ አይደለም። የተለያዩ ሰዎች የተለያየ የአለማመድ መንገድ የሚከተሉ ሲሆን፥ ይህ ግን በመላምቱ ውስጥ ከግምት የገባ አይደለም። ማክላውሊን (ገጽ 35) እንዳቀረበው፥ ጥናቱ መሠረት ያደረገው የምዕላድን ቅደም ተከተል ሲሆን፥ ስለአለማመድ የሚሰጠውም ምላሽ አንድ ወጥ ሊሆን አይችልም። ከዚህ ባለፈ ግን በሐረግና በዐ.ነገር ደረጃ መላምቱን በተግባር ለመፈተሽ የሚያስቸግር ነው። ይህ መላምት በምዕላድ ደረጃ በተደረጉ ጥናቶች ላይ ተመስርቶ የሠነዘረው ንድፈ-ሀሳብ ተቀባይነት የሚያገኝ ቢሆን እንኳን በጣም በተለሳለሰ መልኩ መሆን ይኖርበታል። በእርግጥ በለመዳው ሂደት የተወሰነ ነገር ከሌላው ቀድሞ ሊለመድ ይችል ይሆናል። ይህ ግን እንደክራሽን አባባል ለሁል ጊዜ የሚሰራ አይሆንም።

በክራሽን የቀረበው የሞኒተር መላምት፥ በተለያዩ ምሁራን እንደተፈተሸው በርካታ ችግሮች ያሉበት ነው። ኤሊስ (ገጽ 265) እንደተመለከተው መላምቱ ሕግን በዝርዝር አውቆ ተግባራዊ በማድረግና ሕጉን በዝርዝር ሳይመለከቱ በስሜት እንዳጋጠመ በመጠቀም መካከል ልዩነትን በግልጽ ለማሳየት አያስችልም። በሌላ በኩል፥ መላምቱ በማፍለቅ (production) ደረጃ የሚኖረውን የቋንቋ አጠቃቀም ቢያመለክት እንጂ በተቀባይነት (reception) ደረጃ የሚኖረውን አጠቃቀም አያብራራም። በክራሽን ማብራሪያ ሞኒተር የሚያተኩረው በሕግጋት (አገባብ) ላይ ሲሆን ለቃላት፥ ለዲስኩር፥ ለአነባበብ (pronunciation) ተገቢውን ግምት አይሰጥም።

ክራሽን የዐዋቂዎችንና የሕፃናትን የቋንቋ ለመዳ ልዩነት አስመልክቶ በሰነዘረው አስተያየት ሕፃናት ሞኒተርን ስለማይጠቀሙ በቋንቋ ለመዳው የበላይነት ያላቸው ናቸው። ይሁንና በአገባብና በሥነ-ፍቺ ላይ የተደረጉ ጥናቶች እንደሚደግፉት ዐዋቂዎች በፍጥነትም ሆነ በመጨረሻ ብቃታቸው

የተሻሉ ሆነው ተገኝተዋል፡፡ ሕፃናት የተሻሉ ሆነው የተገኙት በሥነ- ድምጽ ዕድገት ረገድ ነው፡፡ ማክላውሊን (ገጽ 29-30) ይህንኑ መላምት ፈትሾ እንዳስረዳው፥ ሕፃናት የሞኒተር ብቃታቸውን ሳያዳብሩ ቋንቋን የመማር ዕድል አላቸው፤ ነገር ግን ሞኒተርን መጠቀም በእርግጥ የቋንቋ አጠቃቀምን ይነካዋል ወይ? የሚል ጥያቄ ይነሳል፡፡ በርካታ የቋንቋ ተማሪዎች ሕግጋትን ማወቅና መጠቀማቸው ለጥሩ የቋንቋ አጠቃቀም እንደሚረዳቸው ማክላውሊን ይስማማል፡፡ በእርግጥም ብዙዎች እንደሚቀበሉት፥ በዕውቀት ላይ ተመስርተው የሚማሩት የቋንቋ ሕግ በግንዛቤ ላይ ላልተመሠረተ የቋንቋ አጠቃቀም መሠረት ይሆናቸዋል፡፡ ነገር ግን፥ ክራሽን ይህን እውነታ፥ መማር ወደ መልመድ አይሸጋገርም በሚለው ግምቱ ይቃወመዋል ባይ ናቸው፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ ከአፍ መፍቻ ቋንቋ ተናጋሪዎች (ከታላሚው ቋንቋ ተናጋሪዎች) ጋር ግንኙነት ሳይኖራቸው በከፍተኛ ፍጥነት ቋንቋን የሚማሩ ሰዎች ሲኖሩ እነዚህ ሰዎችም ለቋንቋ ለመዳ ዕድል ያልነበራቸው ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ ይሁንና ክራሽን እንዲህ ዓይነቶቹን በሚመለከት በቂ የሆነ ምላሽ አላቀረበም፡፡

የግብዓት መላምት 'የተሟላ ግብዓት' (comprehensible input) ለሚለው መሠረታዊ ጽንሰ-ሀሳብ ብያኔ ስለማይሰጥ፥ ምን ማለት እንደሆነ ለማወቅና በተግባር ለመሞከር የሚቻል አልሆነም ተብሎ ይተቻል፡፡ ሁሉም ዓይነት ግብዓት የተሟላ አይደለም ተብሎ ከተወሰደ ደግሞ ግብዓት፥ የተሟላና ያልተሟላ ተብሎ የሚታወቀው መቼ ነው ለሚለው ጥያቄ መላምቱ አጥጋቢ ምላሽ አይሰጥም፡፡

በክራሽን የግብዓት መላምት ላይ ጠንከር ያለ ተቃውሞ ካነሱት መካከል ስዊይን ይጠቀሳል (ኤሊስ፥ 158)፡፡ በእርሱ የመከራከሪያ ሀሳብ መሠረት የግብዓት መላምት የተሟላ ፍልቃትን (output) ጠቀሜታ ከግምት አላስገባም፡፡ ማፍለቅ (production) በሁለተኛ ቋንቋ ለመዳ ወቅት ያለውን አገልግሎትም አሳንሷል፡፡ የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪው በማፍለቅ ወቅት በርካታ ነገሮችን ይቀስማል፡፡ የተግባቦት ሂደት ሲደናቀፍ አማራጭ እንዲፈልግ ይገፋፋል፤ በአጠቃቀም ሂደት በአገባብ ላይ እንዲያተኩር ይገደዳል፤ የሁለተኛ ቋንቋ ችሎታውንም ለመፈተሽ ይበቃል፡፡ ከዚህና ከመሣሠሉት ሁኔታዎች በመነሳት፥ ላርሰን ፍሪማን፥ ቻውድሮን፥ ከሁሉም በላይ ደግሞ ስዊይን (ኤሊስ፥159) እንደገለፁት የተሟላ ግብዓት ምንም እንኳን የተሟላ ባይሆንም በሁለተኛ ቋንቋ ለመዳ የግድ ወይም በራሱ ብቻ በቂ ላይሆን ይችላል፡፡

በማጣራት መላምት መሠረት ደግሞ፥ ማጣራት (filter) ተማሪው ሊቀስመው የሚችለውን ዕውቀት ሊመጥን፥ ተማሪውም ምን ሊማርና ቋንቋው በምን ያህል ፍጥነት ሊለምድ እንደሚችል ሊወስን ይችላል። ይህ ዓይነቱ የማጣራት ወሳኝነትና ገዳቢነት ሚና በክራሽን ሥራዎች ውስጥ ተድበስብሶ የታለፈ ነው። ማክላውሊን (ገጽ 53) እንዳለው በዚህ ረገድ ምንም ትንታኔ አልተሰጠም። ለምሳሌ ተጽዕኖ የሚያሳድረው ማጣራት፥ (affective filter) የትኛው የቋንቋ ክፍል በቅድሚያ ሊለመድ እንደሚችል አይነግርም።

በክራሽን እምነት፥ በቀላሉ የሚረበሽና ያልተረጋጋ ስሜት ካላቸው አፍላ ወጣቶች ይልቅ፥ ሕፃናት ቋንቋን በፍጥነት የመልመድ ዕድል አላቸው ተብሎ ይገመታል። ምክንያቱም በወጣትነት ዕድሜ ተጽዕኖ የሚያሳድረው ማጣራት ከፍተኛ ስለሚሆን ነው። ይህ በዚህ መልክ ከታየ ግን በዐዋቂነት ዕድሜ ላይ ስሜት ሰከን ይላልና የመልመድ ፍጥነት ሊጨምር ይችላል ወይ? የሚል ጥያቄ ሊነሳ ይችላል። ለዚህ ደግሞ ክራሽን በምርምር የተደገፈ ምላሽ አላቀረበም። ይኸውም አንዳንድ ሕፃናት በለጋ ዕድሜያቸው ለተለያዩ የሥነ-ልቡና ችግሮች ተጋልጠው እያሉ ነገር ግን የቋንቋ ለመዳ ፍጥነታቸው ከሌሎች የዘገየ ሆኖ አይታይም። ስለዚህ እንደነዚህ ያሉ ሕፃናት ተጽዕኖ የሚያሳድርባቸው ማጣራት ከፍተኛ ሆኖ የለመዳ ፍጥነታቸው ይዘገያል ብሎ መቀበል ስሕተት ይሆናል።

## 4. ማጠቃለያ

የክራሽን ሞኒተር ሞዴል የበርካታ መምህራንንና የሥነ-ልሳን ሰዎችን ስሜት የሳበ ሞዴል ነው። በሞዴሉ ላይ ጥልቅ ፍተሻ ባደረጉ አንዳንድ ምሁራን ዓይን ለተግባራዊ ፍተሻ የማይመች፥ በጥልቀት ያልታዩ ወይም በቀላሉ ሊጠቃለሉ የማይችሉ ሁኔታዎች የሚገኙበት ተደርጎ ይታያል። ለዚህም ይመስላል እስካሁን በተደረጉ ጥናቶች ለማረጋገጥም ሆነ ለማፍረስ ያልተቻለ ሞዴል ሆኖ የተገኘው። መላምቱ 'Black box' የሚል ቅጽል ሊሰጠው የበቃውም ከዚሁ በመነሳት ነው።

ይህ ሁሉ ሆኖ ግን በብዙዎች ዘንድ የክራሽን ሞኒተር ሞዴል በዘመናችን ካሉት የሁለተኛ ቋንቋ ለመዳ ንድፈ-ሀሳቦች መካከል ጠንካራ ሆኖ የሚቆጠርና ለበርካታ ሥራዎች መሠረት በመሆን የሚያገለግል ሞዴል ተደርጎ የሚወሰድ ነው ማለት ይቻላል።

## ዋቢ መፃህፍት


Dulay, H. et. al. 1982. *Language TWO*. U.S.A. Oxford: University Press.

Ellis, R. 1985. *Understanding Second Language Acquisition*. Oxford: Oxford University Press.

Krashen, Stephen D. 1982. *Principles and Practice in Second Language Acquisition*. Great Britain: Prentice Hall International Ltd.

Littlewood, William. 1984. *Foreign and Second Language Learning*. Cambridge: Cambridge University Press.

McLaughlin, Barry. 1991. *Theories of Second Language Learning*. Great Britain: Chapman and Hall, Inc.

Tadelle Adamu. 1990. *Individual Differences in Second Language Learning: Informal Context*. University of Reading. (Ph.D. Thesis)